ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ የባለአክሲዮኖች 10ኛ መደበኛ እና 4ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ የጉባኤ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367 (1) ፣ 370 እና 371(1) እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 20 መሠረት የደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 10ኛመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ እና 4ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ሰብሰባ ጥር 17 ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 8:00 ሰዓት እስከ 11:00 ሰዓት በአዲስ አበባ ሳሮማርያ ሆቴል የስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ይካሄዳል::

በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም በሕጋዊ ወኪሎቻችሁ አማካኝነት በተጠቀሰዉ ቀን፣ ሰዓትና ቦታ በጉባዔው ላይ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ የአክብሮት ጥሪውን ያቀርባል::

1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና ዋና መረጃዎች

የማህበሩ ስም፡- ደቦ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ

የማህበሩ ዓይነት፡ በማይክሮ ፋይናንስ ስራ ላይ የተሰማራ አ.ማ

የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት አድራሻ፡ አዲስ አበባ ቦሌ ክ/ከተማ ቲኬ ሕንጻ

የአክሲዮን ማህበሩ ድህረ ገፅ፡ WWW.debomicrofinance.com

የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡ MT/AA/3/0041241/2010

የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ካፒታል፡ ብር 100,000,000

የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ካፒታል፡ ብር 100,000,000

2. የ10ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

1. የጉባዔው ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፣
2. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
3. የውጭ ኦዲተርን መሾም እና ክፍያቸው ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
4. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ነው::

3. የ4ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

1. የጉባዔው ድምፅ ቆጣሪዎችን መሰየም፣
2. የጉባኤውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
3. የአክሲዮን ማህበሩን ካፒታል ማሳደግ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ
4. የአክሲዮን ማህበሩን የመመስረቻ ጽሑፍ ለማሻሻል በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያይቶ ማጽደቅ
5. የጉባኤውን ቃለ-ጉባኤ ማጽደቅ ነው::

4. ማሳሰቢያ

4.1 በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በዋና መ/ቤት ቢሮ ቦሌ ቲኬ ሕንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 111 በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካይም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ በመሆን ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን:: ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል::

4.2 ባለአክስዮኖቹ እና የባለአክሲዮን ተወካይ በጉባዔው ሲገኙ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ዋናውን ከኮፒ ጋር ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል::